13


የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፹፭
አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No.85
ADDIS ABABA 23rd January, 2015


## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፳፩/፪ሺ፮ ዓ.ም


መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......................................ገጽ ፰ሺ፲፬


## CONTENTS

Regulation No. 321/2014


Meles Zenawi Leadership Academy Establishment Council of Ministers Regulation …………Page 8014


የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፩/፪ሺ፮ ዓ.ም

## መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

በትምህርት፣ በሥልጠና፣ በምርምር፣ በምልከታ፣ በትንተና እና በሥርፀት ብቃትና ብስለት ያላቸው ሳይንሳዊና ዘመን ተሻጋሪ ሀሳቦችን በማመንጨት የህዳሴውን መድረክ የአመራር ጥያቄ ሊመልስና የታላቁን መሪ ራዕይ በአስተማማኝ ሁኔታ በማሳካት የህዳሴውን ጉዞ ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚያስችል የአመራር መገንቢያ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፮ እንደተሻሻለ) አንቀጽ (፭) እና (፴፭) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ፫፻፳፩/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.321/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVID FOR THE ESTABLISHMENT OF MELES ZENAWI LEADERSHIP ACADEMY

WHEREAS, it is found necessary to establish leadership institution for the realization of the sustainability of the journey of Ethiopian Renaissance by addressing the question of the leadership of the Renaissance and in achieving the vision of the Great Leader in a reliable manner by generating matured, cultivated, scientific and transcendental thoughts through education, training, research, reflection, analysis and inculcation;

NOW, THEREFORE; this Regulation is issued by Council of Ministers pursuant to Article (5) and (35) of the definition of the powers and duties of the executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No.803/2013).

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Meles Zenawi Leadership Academy Establishment Council of Ministers Regulation No. 321 /2014".


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 17.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩ "ጉባኤ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ መሠረት የተቋቋመው የአካዳሚው ሴኔት ነው፤

፪/ "ሠልጣኝ" ማለት አካዳሚው በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ተመልምሎ፣ሥልጠና ላይ ያለ ሰው ነው፤

፫/ "የአካዳሚው ዘርፍ" ማለት የአካዳሚው አካል የሆነ ዲፓርትመንት፣ ፋኩሊቲ፣ ክፍል፣ማዕከል ወይም ትምህርት ቤትነው፤

፬/ "የአገልግሎት ክፍያ" ማለት አካዳሚው በእውቀት ላይ ተመስርቶ ለሚሰጠው የስልጠና፣ የምርምርና ሌሎች አገልግሎቶች የሚያስከፍለው ክፍያ ነው፤

፭/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ

## ፫. መቋቋም

፩/ መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ (ከዚህ በኋላ "አካዳሚ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ የአካዳሚው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የአካዳሚው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

## ፭. የአካዳሚው መርሆዎች

አካዳሚው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ይመራል፦

፩/ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አመለካከትና አስተሳሰብ መያዝ፤

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires; in this regulation:

1/ "senate" means the senate of the academy established under Article 17 of this regulation;

2/ "trainee" means any natural person who is on training meeting the requirements set by the academy;

3/ "units of the Academy" means department, faculty, part, center or school, established as a constituent units of the academy;

4/ "service fee" means fee to be paid for knowledge based training, research and other services provided by the academy;

5/ "person" means any natural or juridical person;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## MELES ZENAWI LEADERSHIP ACADEMY

## 3. Establishment

1/ Meles Zenawi Leadership Academy (herein after called as the "Academy") is here by established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The academy shall be accountable to the Prime Minister.

## 4. Head Office

The Academy shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

## 5. Principles of the Academy

In pursuance of its objectives the Academy shall be guided by the following basic principles:

1/ uphold democratic and developmental thought and attitude;

፪/ ሁልጊዜ መማር፣ መማማር እና መመራመር፤

፫/ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤

፬/ በብዝሃነት፣ በሕዝብ ወሳኝነትና ተጠቃሚነት ማመን፤

፭/ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፤

፮/ ለውጥን በቀዳሚነት ማራመድ።

## ፮. የአካዳሚው ዓላማዎች

አካዳሚው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የታነፀ፣ የአመራር ጥበቦችን የተካነ፣ በፈጠራ ችሎታው የተመሰገነ፣ ለሕዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ የመስጠት ጥልቅ የአስተሳሰብ ክህሎት ያለው አመራር በየደረጃው ማፍራት የሚችል ጥልቀትና ምጥቀት ባላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ የተመሠረተ አስተማማኝና ሁሉንአቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መዘርጋት፤

፪/ የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ፍልስፍናን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚተገብርና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን በፅኑ መሠረት ላይ በመገንባት ዲሞክራሲያዊ አንድነት እንዲሰፍን የሚደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት በበላይነት የሚመራ የህዳሴዉን አመራር በየደረጃዉ መፍጠር፤

፫/ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ዓለም አቀፋዊ፣ አሕጉራዊና አካባቢያዊ ሥልጠናዎችን በመስጠትና ፎረሞችን በማዘጋጀት ማስፋት፤

፬/ አገሪቱ የጀመረችው የህዳሴ ጉዞ ግቡን እንዲመታ የሕዝቡን ንቅናቄ የሚመራና ከልማታዊ መንግሥት አጠቃላይ ዓላማዎችና መርሆዎች በሚፈልቁ ተልዕኮዎች ላይ በመመስረት የአመራር አቅም ግንባታ ማካሄድ፤

፭/ ለአገራችንና አካባቢያችን ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ተጨባጭ እንድምታ ያላቸውን

2/ continuous learning and research;

3/ respect and ensure the observance of the constitutional order;

4/ believe in diversity, public decisiveness and public benefit;

5/ ensure transparency and accountability;

6/ be vanguard in promoting change.

## 6. Objectives of the Academy

The Academy shall have the following major objectives:

1/ on the bases of scientific and in-depth research, establish reliable and interdisciplinary education and training system that can produce leader at all levels who is shaped in democratic and developmental thought, high level of leadership wisdom, well recognized ability of creativity, critical thinking skill and proactively responding to the public questions;

2/ produce the renaissance leadership at all levels that leads the multifaceted efforts to be exerted to get the democratic unity prevailed and laid on firm foundation by building one political and economic community and implement the developmental and democratic thought and philosophy in a scientific manner;

3/ disseminate developmental and democratic thought and philosophy in a scientific manner by providing international, continental and regional trainings and preparing forums;

4/ conduct leadership capacity building on the basis of missions generated from the general objectives and principles of developmental state in order to lead the mobilization of the public at large and thereby to achieve the goal of the commenced renaissance journey of the country;

5/ by following up, and analyzing the strategic affairs having tangible implications on the peace, development and democracy of our

ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች በመከታተልና በመተንተን የሰልጣኞችን ንድፈ ሃሳባዊና ተግባራዊ አመራር ማሳደግና የታላቁን መሪ አስተምህሮዎች በማስጨበጥ ወደፊት የማራመድ ችሎታቸውን ማሳደግ፤

፮/ ዕውቀትን በማዳበር፣ በማስፋፋትና በማስተላለፍ የሥራ ክቡርነትንና የሕብረተሰብ ብልፅግናን የሚያራምድ አስተሳሰብ እንዲሰርጽና የባህሪ፣ የሥራ ባህል ለውጥና ዕድገት እንዲመጣ የሚጠበቀውን ኃላፊነት መወጣት፤

፯/ ሠልጣኞች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች፣ እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ አንድነት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር።

## ፯. የአካዳሚው ተግባርና ኃላፊነት

አካዳሚው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩/ ለህዳሴው ጉዞ በንድፈሃሳብ ዕውቀት የዳበረ፣ በአመለካከትና ክህሎት የጎለበተ ፣የሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ያለው አመራር ማዘጋጀት፤

፪/ ለአካዳሚው ዓላማ መሳካት በአገራዊ፣ በአካባቢያዊ፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ብቂ ዕውቀት ያላቸው፣ በሥነምግባር የታነጹ፣ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያላቸው ብቁ መምህራን መልምሎ ማዘጋጀት፤

፫/ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና ዙሪያ ለአገር ውስጥ ለውጭ ለተለያዩ የአመራር አካላትና ባለሙያወዎች ሥልጠና መስጠት፤

፬/ የሠልጣኙን ግንዛቤ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድጉና ለችግሮች አፈታት የሚረዱ የተመረጡ ልምዶችን በመቀመር ሥልጠና መስጠት፤

፭/ የመንግሥት ፖሊሲዎችን አተገባበርና ውጤታማነት ማጥናት፤ በቅድመ ሥልጠና፣ በሥልጠና ላይና ከሥልጠና በኋላ ክትትል ማድረግ፣ የብቃትና ጥራት ደረጃን መለካት፣ ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር

country, the region and by upholding the thoughts of the Great Leader, enhance the theoretical and practical leadership capacity of the trainees;

6/ discharge the expected responsibility in bringing about behavioral and working culture change and growth through inculcating dignity of work and dedication for the wellbeing of the society by searching for, cultivating, preserving and transmitting knowledge;

7/ strengthen the awareness of trainees on the rights, equality and democratic unit of Nations, Nationalities and Peoples in accordance with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## 7. Duties and Responsibilities of the Academy

The academy shall have the following duties and responsibilities:

1/ prepare leadership at all levels vigilance on the renaissance journey with enriched knowledge and awareness, matured outlook and skill and having commitment and work motive;

2/ recruit and prepare competent and ethical instructors having democratic and developmental thoughts, equipped with in-depth knowledge of national, regional, continental and international affairs so as to achieve the objective of the academy;

3/ provide training on the context of developmental and democratic thought and philosophy to diverse domestic and international leaders and professionals;

4/ synchronize and use best experiences in conducting training that promote the awareness, knowledge and skill and support the trainees to enhance problem solving skill;

5/ conduct study on the implementation and outcomes of government policies; supervise pre-training, training sessions and post training activities, evaluate efficiency and quality of training and conduct study and research on problems encountered and submit

በማስደገፍ ግኝቶቹን ለሥልጠና በሚመጥን መልኩ በግብዓትነት ማቅረብ፤

፮/ ተመጋጋቢነትና ቀጣይነት ያለው የአመራር ግንባታ ሥርዓት በመዘርጋት በየደረጃው ያለውን አመራር አገራዊ፣ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አውድ ላይ አቅማቸውን መገንባት፤

፯/ ለሥልጠናው አግባብነት ያላቸው የስልጠና አሰጣጥ፣ የምዘናና ግምገማ ሥርዓቶችን ማደራጀት፤

፰/ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በስፋት በመጠቀም የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምር፣ የግንኙነትና የማስረፅ ሥራዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፤

፱/ በአገር ውስጥና በውጭ ካሉ አካዳሚዎች፣ የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አቻ ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር፤

፲/ የጉባኤውን ውሳኔና የሚቀረጸውን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በማድረግ ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን በአግባቡ ላጠናቀቁ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ፣ የባችለር ዲግሪ፣ የማስተርስ ዲግሪ፣ የዶክትሬት(ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሣሣይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ መስጠት፤

፲፩/ የትምህርትና ሥልጠና መጽሔቶች እና ጋዜጦች ማዘጋጀት፤ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ፍልስፍና ላይ ተገቢውን የጥናት፣ የምርምር የምልከታና ትንተና ሥራዎችን ማካሄድ፤ ማሳተምና ማሠራጨት፤

፲፪/ ሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ተልዕኮዎቻቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ተቋማዊ አቅማቸውን በማጎልበትና የስልጠና ፕሮግራሞች ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ እንዲፈፀሙ ድጋፍ ማድረግ፤

፲፫/ በቦርዱ በሚፀድቅ ተመን መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ፤

፲፬/የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤

፲፭/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

the findings thereof in a manner suitable for the respective training contexts;

6/ build the leadership capacity at all levels in national, regional, continental and international arena by establishing complementary and sustainable leadership capacity building system;

7/ organize training methodologies, assessment and evaluation systems relevant to the training;

8/ make efficient and effective activities of education, training, research, communication and inculcation by widely using information technology;

9/ create relationship with inland and foreign counterpart academies, research institutions and those having similar objectives;

10/ award certificates, diplomas, bachelor degree, master's degree, doctorate (PhD) degree or its equivalent for the trainees, subject to senate decisions and curricula to be developed, who have successfully completed their education or training;

11/ prepare journals and news papers on education and training; conduct appropriate study, research, reflection and analysis on the developmental and democratic thought and philosophy; publish and disseminate

12/ enhance the institutional capacities of other similar academies to enable them properly accomplish their missions; and support them to implement the training programs in a complementary manners;

13/ collect service fees for the service it renders in accordance with the rate approved by the board;

14/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

15/ undertake other activities necessary for the attainment of its objectives.

## ፰. የአካዳሚው አቋም

አካዳሚው፦

፩/ መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ ተጠሪነቱ ለቦርዱ የሆነ የትምህርትና ሥልጠና ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፫/ በመንግስት የሚሾሙ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች፤

፬/ የአካዳሚው ጉባኤ ፤እና

፭/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

## ፱. የቦርድ አባላት

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢ፤

፪/ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት፤

፫/ የአካዳሚው ፕሬዚደንት፤

፬/እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ ወይም በአካዳሚው የሚመደብ ፀሐፊ።

## ፲. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩/ የአካዳሚው ከፍተኛው የውሳኔ ሰጭ አካል በመሆን አካዳሚውን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪/ የአካዳሚውን የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምርና የሥርፀት አጠቃላይ ፖሊሲ አቅጣጫ ይወስናል፤

፫/ የአካዳሚውን አደረጃጀት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፤

፬/ አካዳሚው የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የበላይነት በቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ የአመራር ኃይል መፍለቂያ እንዲሆን በበላይነት ይመራል፤

፭/ የአካዳሚውን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

## 8. Organization of the Academy

The Academy shall have:

1/ Meles Zenawi Leadership Academy Board (hereinafter called the "Board");

2/ Education and Training Council accountable to the board (herein after called the "Council");

3/ a President and Deputy Presidents to be appointed by the government;

4/ Senate of the academy; and

5/ the necessary staff.

## 9. Members of the Board

The Board shall have the following members:

1/ the Prime Minister chairperson;

2/ members to be designated by the government;

3/ President of the academy;

4/ a secretary to be assigned by the board or the academy, as may be necessary.

## 10. Duties and Responsibilities of the Board

The Board shall have the following duties and responsibilities;

1/ being the supreme decision making body of the academy direct and oversee the academy;

2/ determine the general policy direction of education, training, research and inculcation of the academy;

3/ issue directives to determine the structure of the academy;

4/ ensure the academies determinedness as an institution where democratic and developmental thought prevail and be a hub for proliferation core leadership;

5/ approve strategic plan of the academy and follow up its implementation

፮/ አካዳሚው ሊከተላቸው ስለሚገቡ ሌሎች ወሳኝና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች አቅጣጫ ይሰጣል።

## ፲፩. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም አንድ ሦስተኛ በሆኑት የቦርድ አባላት ውሳኔ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፪/ ከቦርዱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል።

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፪. የምክር ቤቱ አባላት

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት ሆኖ የአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ የሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ኃላፊዎች እና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ከአካዳሚው እና ከሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።

## ፲፫. የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩/ በስትራቴጂያዊ ጉዳዮች እና ቦርዱ በጋራ መታየት አለባቸው ብሎ በሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ቦርዱን የማማከር፤

፪/ የአካዳሚውንና ሌሎች ተመሳሳይ አካዳሚዎች የትምህርትና ሥልጠና እንቅስቃሴዎች የመከታተያ፣ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ በመሆን የማገልገል፤

፫/ መንግሥት በየበጀት ዓመቱ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት በሚያስቀምጣቸው የትኩረት ነጥቦችና አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት በየደረጃው ያለውን አመራር የንድፈ ሃሳባዊ ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ክህሎት፣ ሥነ-ምግባርና ሌሎች ክፍተቶችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት ለአካዳሚው ቦርድ መነሻ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፤

6/ set direction on the strategic matters that the academy shall peruse.

## 11. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet four times annually; provided, however, that it may have an extraordinary meeting when called by the chairperson or one third of the members of the board.

2/ There shall be a quorum when more than half of the members of the board are present at a meeting.

3/ Decisions of the board shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this article the board may adopt its own rules of procedures.

## 12. Members of the Council

The president of the academy shall be the chairperson and the members of the council includes the deputy presidents, heads of the other similar academies and, representatives from the academy and the other similar academies to be designated by the government and their number shall be determined as may be necessary.

## 13. Duties and Responsibilities of the Council

The Council shall have the following duties and responsibilities:

1/ consult the board on strategic affairs and other matters deemed by the board to be seen jointly;

2/ serve as a forum to follow up, coordinate and evaluate the educational and training activities of the academy and that of other similar academies;

3/ identify theoretical knowledge, Under standing, skill, ethics and other gaps of the leadership at all levels on the basis of focus areas and directions of focus of the government on the process of building developmental democratic system set in each fiscal year and submit recommendation to the board of the academy;

፬/ የአካዳሚውን የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ቀረፃና ትግበራ ተመጋጋቢነትና ቀጣይነት የማረጋገጥ፤

፭/ ሥርዓተ ትምህርቱን ለማጎልበት፣ውጤታማ ሥልጠና ለማካሄድና የአካዳሚውን ተልዕኮ ለማሳካትየሚያስችሉ ልዩ ልዩ ልምዶችን በመቀመር ለሥልጠና ግብዓቶች እንዲያገለግሉ የማድረግ ፣ተፈፃሚነታቸውን የማረጋገጥ፤

፮/ የመስክ ምልከታ ቦታዎችን በመምረጥ ለሥልጠና ግብዓት የማዘጋጀት፤

፯/ በቦርዱ የሚወጡ ልዩ ልዩ የአሠራር መመሪያዎችና አቅጣጫዎች በአካዳሚዎቹ በጥብቅ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤

፰/ የሥልጠናና የምርምር ፍላጐትን መሠረት በማድረግ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ የአካዳሚውን ተልዕኮና ራዕይ በሚያሳካ መልኩ መደራጀቱን የማረጋገጥ፤ በአፈፃፀም የሚታዩ ጉድለቶችን በማጥናትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት መነሻ ውሳኔ ሃሳብ ለቦርድ የማቅረብ፤

፱/ የአካዳሚውን ዓመታዊ የስልጠና ዕቅዶች በመመርመርና በማደራጀት ለቦርዱ መነሻ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ፣ ሲፀድቅም በተቀመጠው አቅጣጫ፣የጊዜ ሰሌዳና አሰራር መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፤

፲/ በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

## ፲፬. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ሲደገፍ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

4/ ensure the formulation and implementation of the training programs of the academy are complimentary to one another and sustainable;

5/ synchronize various best practices enabling to develop the curriculum, to conduct effective training and achieve the mission of the academy thereby use them as input for the training; ensure the implement there of;

6/ select field demonstration places and prepare same for training inputs;

7/ facilitate ways through which the various operational manuals and directives issued by the board of the academy are firmly implemented;

8/ ensure that the preparation of the curriculum is organized in such manner of achieving the mission and vision of the academy; conduct study and submit its recommendation with possible solution to the board of the academy on shortcomings observed during implementation;

9/ examine and organize the annual training plans and programs and submit recommendation to the board; and ensure that it is implemented in accordance with the set direction, schedule and procedure upon approval;

10/ carrying out other activities entrusted to it by the board.

## 14. Meetings of the Council

1/ The council shall meet four times annually; provided, however, extraordinary meetings may be held at any time if the chairperson or one third of the members of the Council request.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the council are present at a meeting.

3/ Decisions of the council shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፲፭. የፕሬዚዳንቱ ተግባርና ኃላፊነት**

፩/ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት የአካዳሚው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ (፯) የተመለከቱትን የአካዳሚውን ተግባራትና ኃላፊነቶች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) አካዳሚው በብዛት፣ በዓይነት፣ በጥራት እና በብቃት የሚፈልገውን ያህል አመራር ማፍራቱን ያረጋግጣል፤

ሐ) መማር ማስተማርን፣ ምርምርንና ሥልጠናን የሚያበረታታ አመቺ ተቋማዊ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ቀጣይነቱንም ይገነባል፤

መ) የአካዳሚው የምርምርና የሥልጠና ተግባራት መንግሥት ቅድሚያ በሚሰጣቸው የሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ላይ ማተኮራቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) የአካዳሚው የትኩረት አቅጣጫ፣ ደንብና መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች አግባብ ባለው የመንግሥት ፖሊሲና ሕግ መሠረት መቀረጸቸውን ያረጋግጣል፤

ረ) የአካዳሚውን ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎች ያዘጋጃል፣ የአካዳሚው የአስተዳደር ሥራዎች በወጡት የደረጃ መለኪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) የአካዳሚውን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በቦርዱ በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሸ) የአካዳሚውን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤

4/ Without prejudice to the provisions of this article the council may adopt its own rules of procedures.

**15. Duties and Responsibilities of the President**

1/ The President of the academy shall be the Chief executive officer of the academy and subject to the general directions of the board, direct and administer the activities of the academy.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the President shall:

a) exercise the duties and responsibilities of the academy stated under Article (7) of this regulation;

b) ensures that the academy prepares leaders in required number, variety, quality and competence in the fields consistent with the needs;

c) create and continuously build conducive institutional environment facilitating learning, training and research;

d) ensure that the academy's education, training and research activities focus on the government priority of the national policies and strategies;

e) ensure that directions of focus,regulation, directives and procedures of the Academy are designed in conformity with the provisions of pertinent laws and Government policies;

f) develop institutional standard of the academy; and ensures that the academy's administrative activities are operated on the basis of the standards;

g) employ and administer the employees of the academy in accordance with the directives approved by the board following the basic principles of the civil service laws;

h) prepare the plans and budget of the academy and implement upon allowed by the board;

ቀ) ለአካዳሚው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

በ) አካዳሚው ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚውን ይወክላል፤

ተ) የአካዳሚውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቸ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮች ያከናውናል።

፫/ ለአካዳሚው ሥራ ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለምክትል ፕሬዚዳንቶች እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ኃላፊነቱን በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ፲፮. የምክትል ፕሬዚዳንቶች ተግባርና ኃላፊነት

የአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንቶች በኃላፊነት የተመደቡበትን ዘርፍ የመምራት፤በአካዳሚው ውስጥ የማስተማርና የማሰልጠን ተግባርና ኃላፊነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተጓዳኝ ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖራቸዋል፦

፩/ ፕሬዚዳንቱ ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የማማከርና የማገዝ፤

፪/ በፕሬዚዳንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፤

፫/ ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ በፕሬዚዳንቱ ውክልና የተሰጠው ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሬዚዳንቱን ወክሎ የመሥራት።

## ፲፯. የጉባኤው አባላት

ጉባኤው፦

፩/ በፕሬዚዳንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ በፕሬዚዳንቱ የሚመደቡ አባላት ይኖሩታል፤

፪/ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል።

## ፲፰. የጉባኤው ተግባርና ኃላፊነት

በቦርዱ የሚሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባኤው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮችን በሚመለከት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፦

i) effect expenditure in accordance with the allowed budget and work program of the academy;

j) represent the academy in its dealings with third parties;

k) prepare and submit to the board performance and financial report of the academy;

l) Carryout such other related activities as are assigned to him by the board.

3/ The President of the academy may delegate part of his duties responsibilities to the Principal Deputy President, Deputy Presidents and other officials of the academy to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the academy.

## 16. Duties and Responsibilities of Deputy Presidents

Without prejudice to their responsibility to direct their respective areas they are assigned, teaching and training activities in the academy the Principal Deputy President and Deputy Presidents shall have the following duties and responsibilities:

1/ advise and assist the President in the exercise of his duties and responsibilities;

2/ exercise duties and responsibilities entrust to them by the President;

3/ the Deputy President delegated by the President shall represent the President in his absence.

## 17. Members of the Senate

The Senate shall:

1/ be presided by the President and have members assigned by the President;

2/ be accountable to the President.

## 18. Duties and responsibilities of the Senate

Without prejudice to the duties and responsibilities assigned to it by the board the Senate shall have the following duties and responsibilities with respect to education and training matters:

፩/ የአካዳሚውን የትምህርትና የሥልጠና ጊዜ ይወስናል፤

፪/ የአካዳሚውን የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችንና ሥርዓተ ትምህርት ይወስናል፤ የትምህርትና የሥልጠና ዘርፎች የሚያካሂዱቸውን የጥናትና ምርምር ሥራዎች ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋል፤ አቅጣጫ ያስይዛል፤

፫/ የሠልጣኞችን አቀባበል፣ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ አወሳሰንን እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

፬/ የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ፣ የባችለር ዲግሪ፣ የማስተርስ ዲግሪ ወይም የዶክትሬት (ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሣሣይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ የሚሰጥበትን አግባብ ይወስናል፤

፭/ የአካዳሚውን ልዩ ልዩ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን ያጸድቃል፤

፮/ በአካዳሚው የሚሰጠውን የትምህርትና የሥልጠና አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫና የሠልጣኞች ምዘና ሥርዓትን ያወጣል፤ አጠቃላይ የመውጫ ፈተና አሰጣጥንና ደረጃዎችን ይወስናል፤

፯/ በቦርዱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የሰልጣኞች አስተዳደር፣ የአካዳሚው የትምህርትና ሥልጠና ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎች የምርጫ ሥነ-ሥርዓት፣ የመምህራን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማጥቅም፣ ዲሲፕሊን፣ ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፣ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰/ በፕሬዚዳንቱ የሚመሩለትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል

## ፲፱. የጉባኤው ስብሰባዎች

፩/ ጉባኤው ለሥራው በሚያስፈልግ መጠን በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ ከጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተጉባኤ ይሆናል።

፫/ የጉባኤው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።

1/ determine the education and training calendar of the Academy;

2/ accredit education and training programs and curriculum of the academy; supervise education and training areas to ensure the relevance quality of education and training; set directions;

3/ examine and determine grievances related to enrollment, education and training standards, and disciplinary measures;

4/ determine conditions on which Certificates, Diplomas, Bachelor Degree, Master's Degree, Doctorate (PhD) Degree or its equivalent are awarded;

5/ approves various education and training programs of the academy;

6/ determine relevance of the education and training, quality assurance and trainees assessment system of the academy; set standard on provision of exit exams;

7/ prepare directive, in accordance with the policies issued by the board, for the administration of the trainees, education and training affairs of the academy, selection procedure for heads of education, employment of instructors, promotion, benefit package, discipline and salary issues and implement same upon approval by the board;

8/ perform other activities referred to it by the President.

## 19. Meetings of the Senate

1/ The Senate may, to the extent necessary for the efficient performance of its activities, meet at any time.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Senate are present at a meeting.

3/ Decisions of the Senate shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ፳. የአካዳሚው ሌሎች ዘርፎች

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፰ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተመለከቱት አካላት እንደተጠበቁ ሆነው የአካዳሚው ልዩ ልዩ የትምህርትና ሥልጠና፣ የምርምርና ስርፀት እና ሌሎች ዘርፎች አመሰራረትና አሠራር በቦርዱ ይወሰናል።

## ፳፩. በጀት

የአካዳሚው በጀት፦

፩/ በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፣

፪/ ከሚሰጠው አገልግሎት ከሚሰበሰብ ክፍያ፣

፫/ ከውርስ፣ ከስጦታ እና ዕርዳታ፣ እና

፬/ ከሌሎች የገቢ ምንጮች፣

የተውጣጣ ይሆናል።

## ፳፪. የሂሳብ መዛግብት

፩/ አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፫. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ ይህንን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም ቦርዱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ አካዳሚው ይህን ደንብና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ መመሪያ ዎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

4/ Without prejudice to the provisions of this Article the senate may adopt its own rules of procedures.

## 20. Other Units of the Academy

Without prejudice to the organs specified under sub-article (1) to (4) of Article 8 of this regulation, the establishment and functions of various educations and training, research and development and other units of the academy shall be determined by the board.

## 21. Budget

Budget of the Academy shall be drawn from:

1/ budget allocated by the government;

2/ proceeds from services it provides;

3/ inheritance, donation and assistance; and

4/ other sources of income.

## 22. Books of Accounts

1/ The Academy shall keep and maintain accurate and complete books of account and financial records.

2/ The books of accounts and financial documents of the academy shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by Auditor General.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 23. Power to Issue Directives

1/ The Board may issue directives for the proper implementation of this regulation.

2/ The Academy may issue directives and manuals for the proper implementation of this regulation and the directives issued under sub-article (1) of this Article.

**፳፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከዛሬ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**24. Effective Date**

This Regulation shall come in to force as of 29th of August, 2014.

**Done at Addis Ababa, this 23rd of January 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት